## ሕገ መንግስቱን፣የምርጫ ሕግንና የስነ-ምግባር ደንብን በመጣስ በመድረክ፣በመድረክ ዕጩዎች፣አባላትና በመራጩ ሕዝብ ላይ እየተሰነዘረ ያለው ሕገ-ወጥ እርምጃ በአስቸኳይ ይቁም!

## ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ የተሰጠ መግለጫ

ዛሬ ዴሞክራሲ እና ከግለሰብ መብት ጀምሮ የቡድን መብቶች ተሟልተው ተከብረዋል እየተባለ በኢሀዴግ በሚነገርላት ሀገራችን፣ የሚባለውና የሚደረገው ለየቅል ሆኖአል:: ላለፉት 18 ዓመታት የመንግስት ስልጣን የጨበጠው ኢሕአዴግ በፍላጎቱ ሥር ያደረገውን ወገን ሁሉ ሲያወድስ፣ ሲመርቅና ሲያሞካሽ በአንጻሩ ደግሞ ጠንከር ያለ ሂስና ተቃውሞ የሚያቀርበውን ወገን፣ ምክንያት እየፈለገ «የአይንህን ቀለም ጠላሁ» በሚል ዓይነት ዘይቤ ሲያብጠለጥል እና ጥቃት ሲሰነዝርበት ይታያል:: ይህም ሁኔታ ከ1997 ዓ.ም ታሪካዊ ምርጫ በኋላ እየተሻሻለ ሳይሆን ይብሱኑ እየሰፋ የሄደ ጉዳይ ሆኗል:: የዚህ ዕጣ ከደረሰባቸው መካከል በጠንካራ ተቃዋሚነቱ በመላ ሀገሪቱና በዓለም ዙሪያ ታውቆ በታሪክ አደባባይ ብቅ ያለው ድርጅታችን «መድረክ» አንደኛውና ዋነኛው ሆኗል:: የመድረክ ጥንካሬ በኢህአዴግና አጋሮቹ ላይ ከፍተኛ ስጋት እንደፈጠረ ከሚያራምዷቸው ፀብ ጫሪ እንቅስቃሴዎቻቸው መረዳት ይቻላል::በዚህ መልክ ከሚከሰተው ውግዘትና ማብጠልጠል ባሻገርም የመድረክ አባላት እየታሰሩ፣እየተሰደዱና አልፎ ተርፎም የመድረክ አባል በሆኑት አቶ አረጋዊ ገ/ዮሀንስ ላይ እንደተፈፀመው የሕይወት መስዋዕትነት ጭምር እየከፈሉ ይገኛሉ::

መድረክ ላይ በየአጋጣሚዎቹ የስም ማጥፋት ዘመቻ እየተካሄደበት፣ ያለ ተግባሩ ተግባር እየተሰጠውና፣ መሰል ተግባር እንዲፈፅሙ በተደራጁ አፍቃሪ ኢህአዴግ በሆኑ የመገናኛ ብዙሀንም ጥላሸት ሲቀባ ውሎ ማደሩ የተለመደ ሆኗል:: የስም ማጉደፊያ ስያሜዎችን ብዛት በቁጥር መግለፅ የሚያታክት ቢሆንም ከብዙ በጥቂቱ ለመጥቀስ-- «የጥፋት ኃይሎች ግንባር፣የኒዎ ሊበራል ወኪሎች ወዘተ» እየተባለ በየአደባባዩ የውግዘት ናዳ ሲወርድ መደመጡ ተለምዷል:: በፓርላማ ሳይቀር «መድረኮች ከጎዳና የተሰባሰቡ ናቸው» የሚል እጅግ አስነዋሪ አባባል ተሰንዝሯል:: እነዚህ ስነ-ምግባርን የጣሱ ፍረጃዎች ከአንድ ሌላውን አክብሮ መከበር ከሚፈልግና ሕዝባዊ ሃላፊነትን መላበስ ከሚገባው ድርጅት የሚጠበቅ አይደለም::

በሌላ በኩል በፖለቲካ መንስዔነት የታሰሩ ብዛት ያላቸው የህሊና እስረኞች በሀገሪቱ ውስጥ የመኖራቸው ጉዳይ በእጅጉ አሳሳቢ ነው::በተጨማሪም የእስር ቤቶቹ አያያዝ ሁኔታ ወ/ት ብርቱካንን ጨምሮ ሌሎችንም እስረኞች ለከፍተኛ የጤና መጓደል የዳረገበት ሁኔታ መኖሩ መገለፁም እጅግ አሳሳቢ ሆኗል:: በመሆኑም መድረክ በዚህ አጋጣሚ ወ/ት ብርቱካንና ተመሳሳይ የጤና ችግር ያለባቸው ሌሎች የህሊና እስረኞች በሙሉ ብቃት ያለው የህክምና እርዳታ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲመቻች መንግስትን አበክሮ ይጠይቃል::

ከዚህ ባሻገር ዛሬ ባለንበት አጠቃላይ ሁኔታ አባሎቻችንና እጩ ተወዳዳሪዎቻችን ላይ ያነጣጠሩ የስነ-ምግባር ደንቡን የሚፃረሩ የማስፈራሪያ፣የማሸማቀቂያና የስነ ልቦና ሰለባ በሚያደርጉ በኢሕአዴግና በመንግስቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት እየተካሄዱብን ይገኛሉ::ከነዚህም መካከል፣

መድረክ
FORUM
The Ethiopian Fed...
Democratic Unity Fo...

1. ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በየአደባባዩ በሚያደርጓቸው ንግግሮችና በሚሰጧቸው ጋዜጣዊ መግለጫዎች ሁሉ በምርጫው ቅስቀሳ ላይ በሚሳተፉ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎችና አባላት ላይ "ሕግ ጥሰዋል" የሚል ክስ መስርተው እንደሚያስቀጧቸው ለዚህም በተለያዩ ስልቶች ማስረጃ እያሰባሰቡ እንደሆነ ደጋግመው እየገለፁ መሆናቸው የምርጫ ስነ-ምግባር ደንቡን የጣሰና ተገቢነት የሌለው ማስፈራሪያ ከመሆኑም በላይ፤ የምረጡኝ ቅስቀሳችን ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የፈጠረ ስለሆነ መድረክ ያወግዘዋል::

2. በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ የማስፈራሪያ ንግግሮች የተደፋፈሩት የኢሕአዴግ ካድሬዎችና የየአስተዳደሩ እርከን ባለስልጣናት በተለያዩ አካባቢዎች በዕጩ ተወዳዳሪዎቻችንና በአባሎቻችን ላይ ድብደባና ሕገ -ወጥ እስራት እየፈፀሙባቸው፤ በንብረታቸውም ላይ ጉዳት እያደረሱና አስተዳደራዊ ማዕቀቦችንም በመጠቀም፤የምረጡኝ ቅስቀሳዎቻችንን እያሰናከሉ ይገኛሉ:: ይባስ ብሎም ዕጩ ተወዳዳሪዎቻችን ከቀጣሪ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ትብብር ሊደረግላቸው ቀርቶ የዓመት ፍቃዳቸውን እንኳን ወስደው ለምረጡኝ ቅስቀሳ እንዳይወጡ እየተደረጉ ናቸው::በዚህ መልክ ኢሕአዴግና መንግስቱ የምርጫን ስነምግባር ደንብ አዋጅ እየጣሱ ይገኛሉ::እነዚህም የሕግ ጥሰቶች እንዲታረሙና አጥፊው እንዲቀጣ በተደጋጋሚ ለምርጫ ቦርድ አቤቱታ አቅርበን መፍትሄ ያጣንባቸው ናቸው ለአብነት ያህልም የሚከተሉትን እንጠቅሳለን::

2.1 በሀዲያ ዞን ዱና ወረዳ በአንሾና ዋስ ገበታ ቀበሌዎች፤ቡሬቡልሻና ቀበሌ፤በኢራና ቀበሌ በሕጉ መሰረት የተጠሩትን ስብሰባዎች አምባጓሮ ፈጥረው በመበተን የመድረክ ዕጩዎችና አባሎች ምንም ዓይነት የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዳያደርጉ መከልከላቸው አንዱ ምሳሌ ነው::

እንዲሁም በሀዲያ ዞን በዕናራ ቀበሌ የክልል ምክር ቤት ዕጩዎች በሆኑት በአቶ ታደሰ ቢንጫሞና በአቶ አንደሞ ዘውዴ እንዲሁም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በዕጩነት በቀረቡት በአቶ አጫሞ ቦቂ ላይ በ24/07/2002 ዓ.ም የድብደባ ወንጀል ተፈፅሟል::

በዚሁ በሀዲያ ዞን ዱና ወረዳ ውስጥ ለክልል ምክር ቤት በእጩነት በቀረቡት አቶ ተስፋዬ ቦቂና የዕጩ ተወካዮች በሆኑት በአቶ ዳዊት ለገሰና በአቶ አየለ ቡፌቦ ላይ በሚሊሻዎች የድብደባ ወንጀል ተፈፅሞ እጅና እግራቸው ተቀጥቅጦ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዋል::

በተጨማሪም በሶሮ 02 ምርጫ ክልል በሊጃ ቀበሌ ውስጥ 1ኛ. አቶ ፍቅሬ መሀመድ 2ኛ. አቶ ዮሀንስ ደባሮ እና 3ኛ. አቶ ፈለቀ የተባሉት የመድረክ አባላትና የምርጫ ቀስቃሾች ከህግ አግባብ ውጭ ታስረዋል::

2.2 በከንባታ ጠንባሮ ዞን በጠንባሮ ወረዳ ለክልል ምክር ቤት በዕጩነት የቀረቡት አቶ አባይነህ ፊታሞ በታጣቂዎች ተደብድበውና ታስረው በስቃይ ላይ ይገኛሉ::

2.3 በምዕራብ ወለጋ ዞን በጻርሶ ወረዳ በ27/07/2002 ዓ.ም አባሎቻችን ለሚመለከተው አካል በማሳወቅ ለምርጫ ቅስቀሳ የጠሩት ስብሰባ በኢሕአዴግ ካድሬዎች እንዲበተን ተደርጓል::

2.4 በ28/07/2002ዓ.ም በምዕራብ ወለጋ ዞን ነጆ ከተማ ተመሳሳይ የብጥበጣ ድርጊት ተፈፅሞ አባሎቻችን የጠሩት ስብሰባ ተበትኗል:: ስለተፈጠረው ችግር አባሎቻችን በወቅቱ ለሚመለከተው

መድረክ FORUM
The Ethiopian Federal Democratic Unity Forum

የመንግስት አካል ቢያሳውቁም ሕገ-ወጦቹ ከፖሊስ አቅም በላይ የሆኑ ናቸው በሚል ማስመሰያ ምንም አይነት የህግ ክስ ለአባሎቻችን ሳይሰጥ ቀርቷል፡፡

2.5 በምዕራብ ወለጋ ዞን በኑኑ ሎሌ ካባ ቁጥር 2 ምርጫ ክልል ስዩ ገባሶ በሚባል ወረዳ ውስጥ የኦፌዲን /መድረክን/ ማሕተም አስመስሎ በተዘጋጀ ማሕተም «ግብር እትክፈሉ» ብሏል በሚል የሀሰት ክስ መንግስትንና የፖለቲካ ፓርቲውን የሚያጋጭ ሕገወጥ ድርጊት ተፈጽሞ በዚሁ ሳቢያ በርካታ አባሎቻችን በቁጥጥር ስር ውለው በምርመራ ላይ ይገኛሉ፡፡

2.6 በገባሶ ወረዳ ከተማ በ24/07/2002ዓ.ም ምሽት የኦፌዴን/መድረክ አባል በሆነው ደገፋ ረጋሳ መኖሪያ ቤት በር ላይ የኦፒዲዮ መፈክር ለመለጠፍ ሙከራ ሲያደርጉ የቤቱ ባለንብረት «አባል ያልሆንኩበት የፖለቲካ ድርጅት በሬ ላይ አይለጠፍም» በማለቱ ተደብ እስከዛሬ በእስር ላይ ይገኛል ::

2.7 በ30/7/2002 ዓ.ም በኢሊባቡር ዞን ጮራ ምርጫ ክልል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በዕጩነት የቀረበችው ወ/ት ቢፍቱ ቀነአ በጅማ አርጆ ካረፈችበት ሆቴል ከሕግ አግባብ ውጭ ተይዛ ከታሰረች በኋላ ተደብድባ ሞባይሏን፣ ቦርሳዋን፣ የእጩነት መታወቂያዋን እና የምርጫ ቅስቀሳ ፖስተሮችንም ጭምር ተዘርፋ በደሌ ተወስዳ ጥለዋት ተገኝታለች፡፡ አቤቱታ የሚቀርበው ለራሳቸው ለወንጀል ፈፃሚዎቹ በመሆኑ በወንወጀለኞቹ ላይ የሚወሰድ እርምጃ ባለመኖሩ የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች እሺ ብሎ ያልተመለሰላቸውን ሁሉ በዱላ እየደበደቡ በሕዝብ ላይ ጉዳት እያደረሱ ናቸው፡፡

2.8 በ2/08/2002ዓ.ም በባሌ ዞን በዶደላ ምርጫ ክልል አቶ በረሶ ዋቤ የተባል የክልል ምክር ቤት ዕጩ ለወረዳው አስተዳዳሪ ልጅ የምርጫ ፖስተር ሰጥተሀል በሚል ሰበብ በሕዝባዊ ስብሰባ ላይ በወረዳው አስተዳዳሪ፣ በፀጥታ ሀይሎችና በፖሊስ ኮማንደሩ የድብደባ ወንጀል ተፈፅሞበታል፡፡

2.9 አርሲ ዞን በዝዋይ ዱግዳ ወረዳ አደሬ ሌጰ ገበሬ ማሕበር ከቀኑ 7:00–8:00 በሚሆንበት ሰዓት የኦህኮ /መድረክ የክልል ዕጩ ተወዳዳሪ የሆነው አቶ መሀመድ ቃሲም ሕዝቡን እያነጋገረ ባለበት ሰዓት በወረዳው አስተዳዳሪ በአቶ አበበ ዱቤ ትዕዛዝ ሰጪነት በሚሊሺያ አራርሶ አቢ እና በሚሊሺያ ማማ የዕጩነት መታወቂያውን ተነጥቆ ከአካባቢው ተባሯል፡፡

2.10 ዕጩዎችንና የዕጩዎች ቤተሰቦችን ማዋከብ፣ ማስፈራራት፣ በጥቅም መደለል ሳይቻል ሲቀር መደብደብ፣ ከስራ ማገድና፣ ቤት አከራዮችን አስፈራርቶ ጽ/ቤት ማዘጋት በኦሮሚያ ክልል በኑኑ ቁምባ፣ በአርጆ ብደጋ ፣ኮሎቦ፣ በጮራ፣ በሻምቡ፣ በአኖ፣ በሚዳቀኝ፣ በጨሊያ፣ በአምቦ፣ በግንደበረትና በቦረና የተፈፀሙ የስነምግባር ጥሰት እርምጃዎች ናቸው፡፡

2.11 ዕጩዎችን ማሰር፣ ለምረጡኝ ቅስቀሳ ሲዘዋወሩ እየተከታተሉ መደብደብ፣ እንቅስቃሴዎቻውን በካሜራ እየቀረፁ ማስፈራራትና፣ በፈጠራ ወንጀል የመክሰስ ድርጊቶች በአምቦ፣ በደንዲ፣ በኢጀሬ፣ በመቂ፣ በሻሸመኔ፣ በቀርሜና፣ በሞያሌና በወላይታ ተፈፅመዋል፡፡

2.12 የመድረክን የምርጫ ምልክት /ፖስተር/ ከቀስታዎች ላይ ቀምቶ በሕዝብ ፊት መቅደድ ወይም ከተለጠፈበት መቅደድና ይባስ ብሎም ጨርሰውን እንዳይለጥፉ መከልከል፣ በመላው መድረክ በሚወዳደርባቸው አካባቢዎች ሁሉ እየተፈፀሙ ያሉ ሕገ ወጥ ድርጊቶች ናቸው፡፡

መድረክ FORUM

2.13 ሌሊት ሌሊት የዕጩዎችን ቤት በመስበር ወይም ቀን በቀን በመንገድ ላይ ጠብቆና በመሳሪያ ሀይል አስፈራርቶ ዕሁፎችንና ሰነዶችን፣ የመቀማት ወንጀሎች በግንደበረት፣ በጮራና፣ በያያ ጉለሌ ተፈጽመዋል:: በተመሳሳይ ሁኔታ የሀሰት ማስረጃ በማዘጋጀት ዕጩዎችን ከውድድር የማሳገድ በአያና ምርጫ ክልል ላይ ተፈጽመዋል::

2.14 በየቦታው ዕጩዎችንና ቤተሰቦቻቸውን ከማስፈራራት አልፎ ሌሊት መኖሪያ ቤቶቻቸውን በድንጋይ መደብደብ ቤት፣ሰብሮ በመግባት ዕጩዎችን መደብደብ ሕገ-ወጥ ወንጀሎች ተፈጽመዋል:: በዚህ ረገድ በ27/7/2002 ዓ.ም በራሱ መኖሪያ ቤት፣ በሚዳ ቀኝ ወረዳ በሚሊሺያ ዘርፍ አባላት ተደብድቦ በአምቦ ሆስፒታልና በጥቁር አንበሳ ሆፒታል ሲረዳ ቆይቶ በ8/8/2002 ዓ.ም በሆስፒታል ሕይወቱ አልፎ በ11/[illegible]/2002 ዓ.ም የተቀበረ ተማሪ ቢያንሳ ጋዲሳና ሆስፒታል ገብቶ ታክሞ የወጣው የጨሊያ ቁጥር 2 ዕጩ ግርማ ነጋሳ ይጠቀሳሉ::

2.15 በምረጡኝ ቅስቀሳ ላይ እያሉ የተደበደቡ፣ ሌሎች ዕጩዎቻችን፣ የአምቦ ቁጥር 1 ዕጩ ብሩ ለገሰ (በሕክምና ላይ ያለ) ፤ ያለም ጤና ዕጩ ተሊላ ብሩ፣ የሰኩሩ ዕጩ አብደላ አባ ፎጊ (በቅስቀሳ ላይ የተደበደበ)፣ የቅስቀሳ ወረቀትና የምርጫ ምልክት በማባዛት ላይ እያለ ተደብድቦ ሆስፒታል የገባው የያያ ጉለሌ እና የደብረሊባኖስ ዕጩ ናኒሳ በቀለ፣ የምርጫ ምልክት በመለጠፍ ላይ እያለ የተደበደበው የወረጃርሶ ዕጩ በላይ ዘለቀና በንቱ ጃንካና አብሯቸው የነበሩት በርካታ ካድሬዎች ናቸው::ባጠቃላይ አባሎቻችን እና ደጋፊዎቻችን በሕገ-መንግስቱ የተደነገጉትን በነፃነት የመምረጥና በመራጩ ሕዝብ መካከል በነፃነት የመንቀሳቀስ ወዘተ የሲቪል መብቶቻቸውን እየተገፈፉ መሆናቸው የአደባባይ ሚስጥር ሆኗል፣ በዚህ ሁኔታ በነፃና ዴሞክራሲያዊ አግባብ የምርጫ ዘመቻ ማካሄድ የሚታሰብ ሆኖ አላገኘነውም::

3. ከፍ ብሎ ከተዘረዘሩት በድርጅታችን፣ በአባላቱና በዕጩ ተወዳዳሪዎቹ ላይ እየተሰነዘሩ ካሉት ሕገ-ወጥ እርምጃዎችና ጥቃቶች በተጨማሪ ገዢው ፓርቲና ካድሬዎቹ በሀገሪቱ ሕጎች የተከለከሉትን ስልቶች በመጠቀም በምርጫው የበላይነት ለመያዝ ይንቀሳቀሳሉ:: ከነዚህ ስርዓት አልበኛ እርምጃዎቻቸው ውስጥም የሚከተሉትን በማሳያነት እንጠቅሳለን:-

3.1 በመላው ሀገሪቱ ውስጥ የምርጫ ስነምግባር ደንብ ክልከላን በመጣስ የኢሕአዴግ ካድሬዎች ለምርጫ ቅስቀሳ የመንግስት ሀብትና ንብረት መጠቀም ላይ ይገኛሉ::

3.2 የመንግስት ስራ ቆሞ የመንግስት ሰራተኞችን ለኢሕአዴግ የምርጫ ቅስቀሳ ማስማራት በየአካባቢው በስፋት ቀጥሏል:: በሌላው አንፃር ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ከቀጣሪ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ትብብር ሊደረግላቸው ቀርቶ ዓመት ፈቃዳቸውን እንኳን ወስደው ለምረጡኝ ቅስቀሳ እንዳይወጡ እየተደረገና ጥቃቅን ምክንያቶችን እየፈለጉ ደመወዝ በመቁረጥና ከስራ ለማባረር እየዛቱ ከፍተኛ ችግር በመፍጠር ላይ ይገኛሉ::

3.3 የምርጫ ካርድን ከመራጩ ሕዝብ እየሰበሰቡ መመዝገብ፣ ዜጎች ኢሕአዴግን እንደሚመርጡ የሚያረጋግጡበትን ፎርም አዘጋጅቶ ማስፈረምና 1ለ5 በሚሉት የጥርነፋ ስልት መዝግቦ በመያዝ ኢህአዴግን እንዲመርጡ ለማስገደድ በመራጩ ሕዝብ ላይ የሥነ ልቦና ጫና ማሳደር በየአካባቢው እየተሰራበት ነው:: በዚህ በማያባራ የኢሕአዴግ ካድሬዎች እንቅስቃሴ መራጩ ሕዝብ እየተዋከበ ይገኛል::

መድረክ FORUM

3.4 በተለይ አርሶ አደሩን በተመለከተ፤በበርካታ የገጠር አካባቢዎች ኢህአዴግን ለመምረጥ እንደሲፍቲኔት ያለ የነፍስ አድን እርዳታ ያሉትን ከማግኘት ውጭ ያደርጋል እየተባለ ለሚሰራጨው ማስፈራሪያ በምዕራብ አርሲ ዞን በሲራሮ ወረዳ ነዋሪ የሆኑትን 48 ገበሬዎችና የቡርጂ ልዩ ወረዳ ነዋሪ የሆኑ 8 አባሎቻችንን ከሴፍቲኔት መሰረዛቸው ማሳያዎች ናቸው፡፡

3.5 ኢህዴግን አይደግፉም ተብሎ በተገመቱ ግለሰቦች ላይ የሚፈፀመው ከማሕበራዊ ኑሮና የእርስ በእርስ ግንኙነት የማግለል ተግባር ይፈጽማሉ፡፡ በዚህ ተፅዕኖ ምክንያት አቋማቸውን የማይቀይሩት እምቢተኞች እየተባሉ በታዋቂ የሀገር ሽማግሌዎችና በሀይማኖት መሪዎች በማስወገዝ ጠርንፎ ድርጅታዊ ሰንሰለት ውስጥ እንዲገቡ ማስገደድ ኢህአዴጋዊ ስልት ሆኗል፡፡

3.6 የተቃዋሚ ፓርቲ ዕጩዎችና ደጋፊዎች በአንድ ቦታ ተረጋግተው እንዳይቀመጡ በስራ ዝውውር ምክንያት ከቤት ንብረታቸው እየተፈናቀሉ በምርጫው የሚወዳደሩበትን አቅም እንዲያጡ በመደረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት የምርጫ ስነምግባር ደንብ ጥሰቶችና የሕግ የበላይነት መጣስ ምክንያት መድረክ ተስፋ ቆርጦ ከምርጫ እንቅስቃሴ እንዲወጣ ያልተፈነቀለ ድንጋይ ያልተበጠሰ ቅጠል የለም፡፡ለምሳሌ የሕዝብ አንጡራ በሆኑ የመገናኛ ብዙሀን የአየር ሰዓት ድልድል መድረክ የስምንት ፓርቲዎች ስብስብ መሆኑ እየታወቀ የተመደበለት የአየር ሰዓት ከአንድ ነጠላ ፓርቲ ጋር እኩል መሆኑ እና በዚህ እዚህ ግባ በማይባል የሬዲዮና የተሌቪዥን የአየር ሰዓት ተጠቅመን ከሕዝባችን ጋር እንዳንገናኝ አቀባው መልኩን እየቀያየረ ሲፈፀሙብን ሰንብቷል፡፡

ስለሆነም

1. በዕጩዎቻችንና በደጋፊዎቻችን ላይ ድብደባ፤እንግልትና ወከባ ሲደርስ፤ ጽ/ቤቶችን የመከራየት መብታችን ሲገፈፍ፤ከመራጩ ሕዝብ ጋር በነፃነት እንዳንገናኝ ሲደረግና ባጠቃላይ የምርጫ ስነ-ምግባር ደንብ ሲጣስ መንግስት ገለልተኛ ሆኖ ሕጋዊ ጥበቃና ከለላ የማድረግ ብቃት ከማጣቱ በላይ ፍላጎትም ባለማሳየቱ፤ ለግንቦቱ ምርጫ የምናደርገው እንቅስቃሴ ከፍተኛ እንቅፋት ስለገጠመው ሁኔታው ባስቸኳይ እንዲስተካከልልን እንጠይቃለን፡፡ በተለይም በዚሁ የምርጫ እንቅስቃሴ ምክንያት በስርዓቱ ታጣቂዎች በደረሰበት ድብደባ ሕይወቱ ያለፈው የተማሪ ቢያንሳ ጋዲሳ አሟሟት በገለልተኛ ቡድን እንዲጣራ አበክረን እንጠይቃለን፡፡
2. ከዚህ በላይ በዝርዝር ከተጠቀሱት ወከባዎች ጎን ለጎን በመድረክ እየተካሄዱ ያሉት ገደብ የለሽ ስም የማጥፋት ዘመቻዎች፤ ማስፈራሪያዎች፤ ዛቻዎችና ማስጠንቀቂያዎች ሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎችን የጣሱና የምርጫ ስነ-ምግባር ደንቡን የሚጻረሩ በመሆናቸው በአስቸኳይ እንዲቆሙ እንጠይቃለን፡፡
3. በሬዲዮና በቴሌቪዥን የአየር ሰዓት ጊዜ አጠቃቀምን በተመለከተ፤ሕገ-መንግስቱን በመጣስ የሚፈፀመው የቅድሚያ ምርመራ አይነቱ አቀባ በአስቸኳይ እንዲቆም መድረክ ይጠይቃል፡፡
4. በመጨረሻም፤ ኢሕአዴግ የምርጫ ዘመቻውን ስራ 1ለ5 በማቀናጀት መራጩ ሕዝብ ላይ ዝርዝር መረጃ መሰብሰብና ከዚያም እያንዳንዱ መራጭ ኢህዴግን ለመምረጥ መስማማቱን

መድረክ
FORUM

በፊርማው እንዲያረጋግጥ የሚያደርገው ወከባ በአስቸኳይ ቆሞ የምርጫው ሚስጥራዊነት እንዲረጋገጥ አበክረን እንጠይቃለን።

**መድረክ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ያሸንፋል!**

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ

ሚያዝያ 14 ቀን 2002 ዓ.ም

አዲስ አበባ